

## Plant seed quality control Directorate/የእፅዋት ዘር ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት

ዳይሬክቶሬቱ በክልሉ ውስጥ ሁለንተናዊ የእፅዋት ዘር ስርዓት እንዲተገበርና ጥራት ቁጥጥር ስርዓትን ለማሻሻል የሚረዱ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ይቀርፃል፤ በእፅዋት ዘር ማምረትና ግብይት ስራ ላይ የተሰማሩ በሀገሪቱ ህግ መሰረት መስራታቸውን ይከታተላል ያረጋገጣል፤ በስራ ክልሉ ውስጥ ዘርን በማባዛት፣በማምረት ፣በማዘጋጀት እና በግብይት ንግድ ስራ ላይ ለተሰማሩ የግልም ሆነ የመንግስት ዘር አምራቾችና አቅራቢዎች ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ያድሳል፣ ህጋዊ አሰራሮችን ያልተከተሉ ሆነው በሚገኙበት ጊዜ ይሰርዛል፡፡ በስራ ክልሉ ውስጥ በዘር ማምረት፣ በማባዛት ወይም በግብይት ስራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው አስተማማኝ የጥራት ቁጥጥር እየተካሄደበት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በዘር ማምረት ስራ ላይ ለተሰማሩ አካላትና ለጥራት ቁጥጥር ባለሙያዎች ለጥራት ቁጥጥር የሚያግዙ የአቅም ግንባታ ስራዎች መካሄዳቸውን ይከታተላል፡፡ በክልሉ ውስጥ በሚመረቱ ዘሮች ላይ በመስክና በክምችት ናሙና ተወስዶ እንዲመረመር በማድረግ ጥራቱን ያረጋግጣል፣ የሁሉንም ዘር ደረጃዎች መለያ ምልክት (ታግ) ለይቶ ለተጠቃሚዎች እስኪደርስ ድረስ ሂደቱን በባለቤትነት ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፡፡ ለዘር አምራቾች፣አዘጋጆች አቅራቢዎች፣ ሻጮችና ተጠቀሚዎች፤ በጥራት ደረጃዎች አጠባበቅና በአዋጆች በማስፈፀሚያ ደንቦችና መመሪያዎች አተገባበር ረገድ ስልጠናዎች እንዲሰጡ፤ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብሮች እንዲነደፉ ያደርጋል፡፡ የጥራት መጓደልን አስመልክቶ ከተጠቃሚዎች ለሚነሱ ማናቸውም ቅሬታዎች የተጠኑ ምላሾችን ይሰጣል፡፡ ምርታማነታቸውና ውጤታማነታቸው የወረደ ዘሮች ከስርጭት እንዲወጡ ያደርጋል፡፡ በመስክና በክምችት የጥራት ቁጥጥር ተካሂዶባቸው የጥራት ደረጃ መስፈርቶችን ያላሟላ ዘርን አጠቃቀምና አወጋገድ ይከታተላል፣ የዘርጥራት ቁጥጥርና የማረጋገጥ ጉዳዮችን አስመልክቶ የስራ ክልሉን ይወክላል፡፡

የዘር ጥራት ቁጥጥርን ተግባር ለማዘመን የዘር ብዜት ማሳዎችን በጂ ፒ ኤስ በመለካት ትክክለኛ መረጃውን በዲጂታል አንፎሜሽን በመመዝገብ አስፈላጊውን መረጃዎች በበይነ መረብ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፤ የእጽዋት ዘር ማምረት፣ ማዘጋጀትና ማከፋፈል ላይ የተሰማሩ ባለድርሻ አካላት የአገልግሎት አሰጣጥ በተመለከተ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ እና መረጃ በማንኛውም ጊዜ ሊያገኙ የሚችሉበት አሰራር ተግባራዊ እንዲሆነ ያደርጋል፤ ክልሉ ጥራቱን የጠበቀ ዘር በማቅረብ ተዋዳዳሪና ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ በዘርፉ ያሉ የጥራት ቁጥጥር መርሆዎችን እና ስምምነቶች እንዲተገበሩ

ያደርጋል፤ ከሌሎች ክልሎች ወደ ክልሉ ውስጥ የሚገቡ የዕጽዋት ዘሮች ወደ አርሶአደሩ ከመድረሳቸው በፊት የብቃት ማረጋገጫ በተሰጣቸው አቅራቢዎች የገቡ መሆናቸውንና የዘር ጥራት መስፈርቶችን ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤ በክልሉ ውስጥ ተባዝተው ለሌሎች የሚላኩ የዕጽዋት ዘሮች በጥራት መስፈርቶች መሰረት መባዛታቸውን በመስክ ኢኒስፔክሽን በመሰራት መስፈርቱን ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤ በዘር ጥራት ላይ ከሚመለከታቸው ጋር በጋራ ይሰራል፤ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤ አዳዲስ የዘር ጥራት ፍተሻ አሰራሮችን በመቀመር ለሌሎች ያስተዋውቃል፤ ያስፋፋል፤ ለተግባራዊነታቸውም ክትትልና ድጋፍ ያደረጋል፤ በተለየ ሁኔታ የክልል ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው አካላት እና ድጋፍ ለሚጠይቁ ድርጅቶች ሁለንተናዊ አቅማቸውን ለማሳደግ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል። በክልሉ ውስጥ የሚካሄድ ህገ-ወጥ ዝውውርን ይከታተላል፤ ህገ-ወጦችን ከሚመለከታቸው የህግ አካላት ጋር በመሆን ለህግ እንዲቀርቡ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

በመሆኑም ዳይሬክቶሬቱ በአሁኑ ሰዓት የመስክ ሰብል፣ የአትክትና ፍራፍሬ፣ የደንና መኖ ዘር ጥራትን በመስክና በላብራቶሪ የመቆጣጠር ስራ እያከናወነ ይገኛል። በተጨማሪም በእፅዋት ዘር ማባዛት፣ ማምረት፣ ማዘጋጀት እና በግብይት ንግድ ስራ ላይ ለተሰማሩ የግልም ሆነ የመንግስት ዘር አምራቾችና አቅራቢዎች ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፣ የማደስ፣ እንዲሁም ህጋዊ አሰራሮችን ያልተከተሉ ሆነው በሚገኙበት ጊዜ የመሰረዝ ስራ እያከናወነ ይገኛል።

**የዳይሬክቶሬቱ አድራሻ**

- ባህርዳር ከተማ : ፋሲሎ ክፍለ ከተማ፡ እንስሳትና አሳ ሃብት ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ
- የቢሮ ስልክ ቁጥር : +251582265830

**የዳይሬክቶሬቱ ዳይሬክተር**

- ስም: ጉርሜሳ እጀታ ደያ
- ስልክ ቁጥር: 0918803126
- ኢሜል: amanelge@gmail.com